የ PepsiCo የስነ-ምግባርና የታማኝነት ባህልን ለማስጠበቅ ሲሉ በቅን ልቡና የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ከየትኛውም ዓይነት የብቀላ ተግባር ለመጠበቅ PepsiCo ቁርጠኛ ነው።

**ወሰን**

ይህ ዓለምአቀፍ የፀረ-ብቀላ ፖሊሲ በሁሉም የPepsiCo ተባባሪዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፣ እነርሱም የPepsiCo የተዋሃዱ ቅርንጫፎች ሰራተኞችን እንዲሁም ለPepsiCo አገልግሎት ሲሰጡ ተቋራጮችን ይጨምራል።

**በቀል የተከለከለ ነው**

PepsiCo ተባባሪዎቹ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የPepsiCo የስነምግባር እና የታማኝነት ባህልን የሚደግፉ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ላይ ብቀላ መፈጸምን በጥብቅ ይከለክላል። ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የ PepsiCo የስነ-ምግባርና የታማኝነት ባህልን ደግፈዋል የሚባለው በቅን ልቡና የሚከተሉትን ሲያደርጉ ነው፡-

- የ PepsiCo ዓለም አቀፍ የአሰራር ደንብ (“ደንብ”)፣ ፖሊሲዎች ወይም ሕግ ላይ በተጨባጭ የተፈጸመ ወይም የተጠረጠረ ጥሰትን በደንባችን ውስጥ ከተገለጹት የሪፖርት ማድረጊያ መንገዶች በአንዱ አማካይነት ወይም ለመንግስት ባለስልጣናት ሪፖርት ካደረጉ፣ ሪፖርት የማድረግ ፍላጎትዎን ከገለጹ እና/ወይም ሌላ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሪፖርት እንዲያደርግ ካገዙ፤
- ተጨባጭ ወይም ተጠርጣሪ ጥሰትን በተመለከተ ለውስጣዊ ወይም መንግስታዊ የምርመራ ስራ መተባበር ወይም በውስጣዊ ወይም መንግስታዊ የክስ ሒደት ውስጥ መሳተፍ፤ ወይም
- ስለ አንድ የንግድ ስራ አሰራር፣ ውሳኔ ወይም እርምጃ ጥያቄ መጠየቅ ወይም አሳሳቢ ጉዳይ ማንሳት ወይም ምክር መጠየቅ።

**የብቀላ ትርጉም**

ለዚህ ፖሊሲ አላማዎች ሲባል፣ የብቀላ እርምጃ ማለት አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የPepsiCo የስነ-ምግባርና ታማኝነት ባህልን እንዳይደግፍ የሚያደናቅፍ ወይም የሚቀጣ ማንኛውም ተግባር ነው። ይህም የሚያካትታቸው፡-

- አንድን ግለሰብ የስራ ዕድል የሚያሳጣ ወይም በሌላ መልኩ ግለሰቡ እንደ PepsiCo ተቀጣሪነቱ ወቅታዊ ወይም የወደፊት ሁኔታው ላይ ወይም ከPepsiCo ባለው ወይም ባላት የቅጥር ደንቦች ወይም ሁኔታዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር ማንኛውም ሆን ተብሎ የሚወሰድ እርምጃ።
- ኮንትራክተሩ ወይም አቅራቢው አገልግሎቶችን ወይም እቃዎችን ለPepsiCo ለማቅረብ እድሉን የሚነፍግ ወይም በሌላ መንገድ የእነዚያን አገልግሎቶች ወይም ዕቃዎች አቅርቦት ውሎች ወይም ሁኔታዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያደርግ ሆን ተብሎ የሚወሰድ እርምጃ።
- ያሳሰበውን ጉዳይ በቅን ልቡና ተነሳስቶ ለPepsiCo ወይም ለመንግስታዊ ኤጀንሲ ያሳወቀ ወይም በምርመራ ሂደት ላይ የተሳተፈ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ላይ የሚወሰድ ህጋዊ እርምጃ፣ ወይም ሆን ተብሎ የተደረገ የንግድ ወይም ኢኮኖሚያዊ ብቀላ፣ መልካም ስም ላይ ጉዳት ማደረስ፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት ወይም ጥቃት።

ይህ ፖሊሲ እንደ PepsiCo ተባባሪ የስራ አፈጻጸም ላይ የተመሰረቱ እርምጃዎች ያሉ የኩባንያውን መደበኛ፣ ሕጋዊ፣ የንግድ አሰራሮችን አይገድብም።

**ጥሰቶችን ሪፖርት ስለማድረግ**

በዚህ ፖሊሲ ላይ እንደተፈጸሙ የተጠረጠሩ ጥሰቶችን ለሰው ሃብት ተወካይ፣ ወይም ለየትኛውም የሕግ ክፍል አባል ወይም ለሕግ ተገዥነትና የስነ-ምግባር መምሪያ ሪፖርት እንዲያደርጉ ይጠበቅብዎታል። እንደአማራጭም፣ የተጠረጠሩ ጥሰቶችን በSpeak Up የስልክ መስመር በኩል ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ (http://www.pepsicospeakup.ethicspoint.com)።

**ለውስጣዊ አካላት ወይም ለመንግስት ሪፖርት ማድረግ ላይ የተጣለ ገደብ የሌለ ስለመሆኑ**

በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ወይም በሌላ ቦታ የተካተተ ድንጋጌ በስራ ላይ እያሉም ሆነ ከስራ ከለቀቁ በኋላ በኩባንያው ውስጥ ሊፈጸሙ የሚችሉ የደንብ ወይም የሕግ ጥሰቶችን በተመለከተ ተባባሪዎች የሚያሳስባቸውን ጉዳይ ከማሳወቅ አይከለክልም።

በተጨማሪም፣ በዚህ ፖሊሲ ወይም በሌላ በማንኛውም የ PepsiCo ፖሊሲ ወይም ስምምነት ውስጥ ያለ ድንጋጌ ሰራተኞች በቅጥር ጊዜያቸው ወይም ከዚያ በኋላ በደንቡ ወይም በተፈጻሚ ሕግ ላይ የተፈጸሙ ጥሰቶችን የማሳወቅ፣ ለመንግስታዊ ድርጅቶች መረጃ የመስጠት፣ ለመንግስት ድርጅቶች ቅሬታ የማቅረብ ወይም በመንግስት ድርጅት ምርመራዎች ወይም የክስ ሒደቶች ውስጥ የመሳተፍ ችሎታቸውን አይገድብም።

**የፖሊሲ ጥሰት መዘዞች**

ይህንን ፖሊሲ የሚጥስ ማንኛውም የ PepsiCo ሰራተኛ፣ ከስራ እስከመባረር ጨምሮ፣ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል። በአንዳንድ ጊዜያት፣ የተከለከለ ብቀላ ከህጉ በተቃራኒ ሊቆምና የሰራተኛው በወንጀል ወይም በሲቪል ቅጣቶች የመቀጣት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

በተከለከለ ተግባር ውስጥ የተሰማራ ማንኛውም ስራ ተቋራጭ ለኩባንያው የስራ ተቋራጭ አገልግሎቶችን እንዳይሰጥ ሊታገድ ይችላል።

**ጥያቄዎች አሉዎት**

ስለ Speak Up ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ ይህን ይመልከቱ Speak Up በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች። ይህን ፖሊሲ የተመለከቱ ማናቸውንም ጥያቄዎች ለሴክተርዎ፣ ለክልልዎ ወይም ለቢዝነስ ክፍል የሕግ ማስከበርና የስነ-ምግባር ኦፊሰር ማቅረብ ይችላሉ። እንደ አማራጭም፣ ለዓለም አቀፍ የሕግ ተገዥነትና ስነ-ምግባር መምሪያ በቀጥታ አድራሻ ኢሜይል መላክ ይችላሉ PepsiCoComplianceandEthics@pepsico.com።